የ ድ ሬ ዳ ዋ   አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ ጣ

# DIRE NEGARIT GAZETA

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

አንደኛ ዓመት ቁጥር6
ድሬዳዋ __ቀን 2001

በድሬዳዋ አስተዳደር
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No.6
DIRE DAWA___2008

## አዋጅ ቁጥር 6/2001

### የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር የድሬዳዋን ምክር ቤትን ለማፍረስ የወጣ ረቂቅ አዋጅ

የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር የድሬዳዋ ምክር ቤት የተቋቋመበትን ዓላማ ያሳካና የሚሊኒየሙም በዓል የተጠናቀቀ በመሆኑ ምክር ቤቱን ማፍረስ በማስፈለጉ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 12/1/ /ሀ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ አዋጅ «የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር የድሬዳዋ ምክር ቤት ማፍረሻ አዋጅ ቁጥር 6/2001» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>መፍረስ</u>

   በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር ደንብ ቁጥር29/1999 ተቋቁሞ የነበረው የኢት ዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር የድሬዳዋ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ፈርሷል፡፡

3. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

1. በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር ደንብ ቁጥር29/1999 ተቋቁሞ የነበረው የኢ ትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር የድ ሬዳዋ ምክር ቤት መብትና ግዴ ታዎች በአዋጅ ቁጥር2/1996 መሠረት ለተቋ ቋሙት ለሚከተሉት የአስ ተዳደሩ መሥ ሪያ ቤቶች ተላልፈዋል፡፡
   ሀ. ከንቲባው ጽ/ቤት
   ለ. ማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት ቢሮ
   ሐ.ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ
   መ. ገጠር ልማት ቢሮ
   ሠ. ጤና ቢሮ
   ረ. ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
   ሰ. ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ
   ሸ. ትምህርት ቢሮ
   ቀ. ሴቶች ጉዳይ ቢሮ
   በ. የከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
   ተ. ፍትህ፣ፀጥታና የሕግ ጉዳዮች ቢሮ
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ላይ የተገለፀውን ድንጋጌ የማስፈፀም ኃላፊ ነት የአስተዳደሩ ካቢኔ ይሆናል፡፡

4. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከ__ ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ድሬዳዋ __ ቀን 2001 ዓ.ም.

አደም ፋራህ

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ